UW Medicine
UNIVERSITY OF WASHINGTON
MEDICAL CENTER

# ቀጣይ የሆነ የነርቭ መዘጋት

*ህመምን ለመቆጣጠር*

*ይህ ሰነድ ቀጣይነት ያለው የነርቭ መዘጋት ቱቦ እንዴት እንደሚሰታ እና ቱቦው ሲደረግ ምን እንደሚጠበቅ ያብራራል።*

ለጠቃሚ ቪዲዮዎች ስልክዎን ተጠቅመው ይህንን የኪው አር ኮድ ስካን ያድርጉ


### ቀጣይ የሆነ የነርቭ መዘጋት ምንድነው?

ቀጣይ በሆነ የነርቭ መዝጋት ቀዶ ጥገናዎ/ ህክምናዎ አነስተኛ የፕላሰቲክ ቱቦ(ካታተር) ህመምን ለመቆጣጠር ይደረግልዎታል።ቱቦው /ካተተሩ ስሜትን እና እንቅስቃሴን ከሚቆጣጠሩት ነርቮች አጠገብ በሚያሠቃየዎ እግር ውስጥ




## ምን መጠበቅ አለብኝ ?

- የነርቭ ዘጊው ቱቦ/ካታተር ህመምዎን ሙሉ በሙሉ አያስወግድም ።ነገር ግን ቱቦው በሚሰራበት ወቅት ብዙ የህመም ማስታገሻ መድሃኒት መውሰድ አይጠበቅብዎትም።
- ቀጣይነት ባለው መልኩ ህመምዎን ለማሰታገስ መሳሪያው መድኃኒቱን በዝግታ የፍሰት ፍጥነት ይረጨዋል። የሚያስፈልግዎ ሆኖ ከተሰማዎ ተጨማሪ የማደንዘዣ መድሃኒት ለመስጠት የምትጫኑት ቁልፍ አለ።
- ቱቦው/ካታተሩ የተቀመጠበት እግር የደነዘዘ እና ደካማ ሊሆን ይችላል። ሙሉ ክብደትዎን በእሱ ላይ ማድረግ አይችሉም።
- በሂደት መንፊያው /ፓምፑ በዝግታ ቅርፁን ሊያጣ እና ጠፍጣፍ ሊሆን ይችላል። ይህም 2 ወይም 3 ቀናትን ሊወስድ ይችላል። ፓምፑ ባዶ ሲሆን በውስጡ ጠንካራ ንጣፍ (በገጽ 2 ላይ ያለውን ምስል ይመልከቱ) ሊያዩ ይችላሉ።
- የተገጠመለዎት ቱቦ /ካታተር ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ የክብካቤ ቡድን አባል በቋሚነት ከእርስዎ ጋር የሚገናኝ ይሆናል።
- ዶክተርዎ እንዲያደርጉ እስካልነገረዎት በቀር የፍሰት ፍጥነት ማስተካከያዉን አይቀይሩት።




*የፊኛው መጫኛ(ቁልፍ) አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ የማደንዝዣ መድሃኒት ለመጨመር የሚያገለግል ነው።*



**ፊኛ (ፓምፕ) ባዶ ሲሆን**

ይህ ስዕል ከ ሃልያርድ ጤና ድርጅት በተገኘ ፈቃድ ጥቅም ላይ ውሏል

## ተጨማሪ የማደንዘዣ ዶዝ/መጠን እንዴት ለራሴ መጨመር እችላለሁ?

1. የፊኛው ቁልፍ/በለስ ቦታው ላይ እስኪቆለፍ ድረስ ወደ ታች  ይጫኑት.
2. መድሃኒቱ መምጣት ይጀምራል። ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ ይህ የፊኛ ቁልፍ/በለስ ወደ ላይ ብቅ ይላል።ከዛም በኋላ ፊኛው መነፋት ይጀምራል።
3. በጎን ያለው የመጨመሪያ ቢጫ የፊኛ አመልካች  ምን ያህል መድሃኒት
4. በፊኛው ውሰጥ እንዳለ ያሳያል። የመጨመሪያ ቢጫ የፊኛ አመልካቹ እላይ ከሆነ ያለው ሌላ ሙሉ ዶዝ መድሃኒት እንዳለ ያመለክታል። ይህም 30 ደቂቃ አካባቢ ይወስዳል።
5. በፊ የተሞላው መድሃኒት የማለቂያ ግዜው ሳይደርስ ፊኛውን መጫን የዶዙን የተወሰነ መጠን ብቻ ያገኛሉ።

## የራስ ክብካቤ

- ሁልጊዜ የነርብ መዘጋት ያለተበትን  እግርዎን ይጠብቁ። ከሙቀት ፣ ከቀዝቃዛ ፣ ከጠንካራ ወይም ከሹል ቦታዎች ይጠንቀ። እግርዎ ህመም ወይም ጫና ስለማይሰማው(ሰለደነዘዘ) በቀላሉ ሊጎዱ ይችላሉ።
- ሲንቀሳቀሱ ይጠንቀቁ። የሰውንትዎ ሚዛን ሊነካ ይችላል።
- ቱቦውን/ ካቴታተሩን አይጎትቱ።
- ይህ የነርብ መዝጊያ ተደርጎለዎት  እያለ ሲቆሙ ወይም ሲራመዱ  ሁል ጊዜ አንድ ሰው እንዲረዳዎት ያድርጉ። ብቻዎን ለመቆም ወይም ለመራመድ ከመሞከርዎ በፊት ቴራፒው እስኪቆም ድረስ እና ሙሉ ስሜት እና ጥንካሬ እስኪያገኙ ድረስ ይጠብቁ።
- ቱቦው /ካታተሩ በእግርዎ ውስጥ ካለ በእግርዎ ሲራመዱ አልያም ሲቆሙ ሁልጊዜ አጋዥ መሳሪያዎችን ለምሳሌ እንደ ጉልበት ማነቃቂያ፣ ክራንች ወይም መራመጃ (ዎከር) ይጠቀሙ።
- ስለ አቀማመጥ/ኣቋቋም እና እንቅስቃሴ የዶክተርዎን መመሪያዎች ይከተሉ።
- የቱቦውንን/ ካታተር ማስገቢያ ቦታ እና ማሰሪያ እንዲደርቅ ያድርጉ።


Anesthesia and Pain Medicine | Harborview Medical Center
325 Ninth Ave, Seattle WA 98104 | 206.999.0992

## የጎንዮሽ ጉዳቶች ይኖሩት ይሆን?

ሁሉም ህክምናዎች/ቀዶ ጥገናዎች አደጋዎችን፣ የጎንዮሽ ጉዳቶች እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች አሏቸው። በጣም የተለመደው የጎንዮሽ ጉዳት በቱቦው/ካቴተር ቦታ ላይ የአጭር ጊዜ ህመም ነው።

አንዳንድ ጊዜ በጣም ትንሽ መጠን ያለው የማደንዘዣ መድሃኒት በፋሻው ስር ሊፈስ ይችላል። ነገር ግን ይህ ምንም የሚያስጨንቅ አይደለም ። ሌሎች አደጋዎች ኢንፌክሽን፣ብክለት፣ የደም መፍሰስ እና የማያቋርጥ መድከም/መዛል ያካትታል። ከዚህ ህክምና/ቀዶ ጥገና ሂደት ውስጥ ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች እና ችግሮች የሚያጋጥሙት በጣም አልፎ አልፎ ነው።

## መንፊያው ባዶ ሲሆን ቱቦውን/ካታተሩን እንዴት አወጣዋለሁ ?

1. ይቀመጡ እና ፋሻውን ከቱቦው/ካታተሩ ላይ ይፍቱት። መቀሶችን አይጠቀሙ።
2. በቆዳዎ አጠገብ ያለውን ቱቦ/ ካታተር በደንብ ይያዙ ፤በእርጋታ እና ዝግ ባለ ጉተታ ከቆዳዎ ላይ ያንሸራትቱት። ቱቦው/ካታተሩ በቀላሉ መውጣት አለበት።በዚህ ወቅት ምንም ህመም ወይም በጣም ትንሽ ህመም ወይም ይገባል።
3. መጎተት ሲጀምሩ ድንገተኛ ኃይለኛ ህመም ከተሰማዎት ያቁሙ። መመሪያ ለማግኘት ይደውሉልን (ስልክ ቁጥራችንን በ "ጥያቄዎች" ሳጥን ውስጥ ይመልከቱ)
4. ቱቦውን /ካታተሩን ካወለቁ በኋላ ጫፉ ላይ የጠቆረ ምልክት መኖሩን ይፈትሹ። የጠቆረ ምልክት ካላዩ ወደ አቅራቢዎ ይደውሉ።
5. ቱቦውን/ካታተሩን ካስቀመጡ በኋላ ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያው ይርጨት
6. ቱቦው/ካታተሩ በነበረበት ቦታ ላይ ትንሽ ባንዴጅ ያኑሩበት።
7. የቱቦ/ካታተር አወጋገድ ቪዲዮን ለመመልከት እባከዎን *www.myon-q/faqs.aspx* ን ይጎብኙ።

### ጥያቄዎች?

ጥያቄዎቻቹህ ጠቃሚዎች ናቸው።

ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት ሐኪምዎን ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይደውሉ።

- ❑ የሃርበርቪው ክልላዊ የማደንዘዣ አገልግሎት፡ በሳምንት ቀናት ከጥዋቱ 8፡00 እስከ ምሽቱ 5፡00 ስዓት በ 206.999.0992 ይደውሉ።
- ❑ ከሰራ ውጭ እና በሳምንቱ መጨረሻ እና በበዓላት ቀን፦ እባክዎን ነርሶችን ለማነጋገር በON-Q የ24-ሰዓት የምርት ድጋፍ የስልክ መስመር 800.444.2728 ይደውሉ።

**መቼ መደወል እንዳለበዎት**

ከእነዚህ ከባድ ምልክቶች አንዱ ካለብዎት ወዲያውኑ ይደውሉልን፦

- የደነዘዘ ከንፈር
- በአፍዎ ውስጥ የብረት ጣዕም
- ጆሮዎ ላይ የቃጭል/ደወል ጩኸት
- ከባድ የማዞር ስሜት
- ማቅለሽለሽ እና ማስታወክ

© University of Washington Medical Center
Published PFES: 2017, 2020, 2022. 2023
Clinician Review: 10/2022
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu

UW Medicine
HARBORVIEW MEDICAL CENTER

# Continuous Nerve Block

*For pain control*

*This handout explains how a continuous nerve block catheter works and what you can expect when it is placed.*

*Scan this QR code with your phone for helpful videos.*


## What is continuous nerve block?




In your continuous nerve block procedure, a small plastic tube (catheter) will be placed to help with pain management. The catheter is placed close to the nerves that control feeling and movement in the painful limb. A small device pumps numbing medicine through the catheter to control your pain.

## What should I expect?

- The nerve block catheter will not take away all your pain. But, you will not need to take as many pain pills while it is working.
- The device automatically pumps the medication at a slow flow rate for continuous pain relief. There is a button you can press to give yourself an extra dose of numbing medication if you feel you need it.
- The limb where the catheter is placed will be numb and may be weak. You may not be able to put all your weight on it.
- Over time, the pump will slowly lose its shape and flatten. This should take 2 to 3 days. When the pump is empty, you will see a hard core inside (see the image on page 2).
- A care team member will routinely contact you while your catheter is in place to make sure it is working safely.
- Do not change the flow rate dial unless your doctor tells you to.




*The bolus button is used to give an extra dose of numbing medication, if needed.*

## How do I give myself an extra dose of numbing medication?

1. Press down on the bolus button until the button locks into place.
2. The medicine will be delivered. The bolus button will pop up after a few minutes. The bolus will then begin to fill.
3. The orange bolus refill indicator on the side shows you how much medicine is in the bolus.


Anesthesia and Pain Medicine | Harborview Medical Center
325 Ninth Ave, Seattle WA 98104 | 206.999.0992




*The pump when it is empty.*

*Image used with permission from Halyard Health.*

4. Another full dose of medicine is available when the orange bolus refill indicator is at the top level. This will take about 30 minutes
5. Pressing the button before the end of the refill time will give you only part of the medicine dose.

## Self-care

- Always protect your limb that has the nerve block. Be careful with hot, cold, hard, or sharp surfaces. You can easily get hurt since your limb does not feel pain or pressure.
- Be careful when you move. Your balance may be affected.
- Do not pull on the catheter
- Always have someone help you when you stand or walk while you have this nerve block. Wait until the therapy is stopped and you have regained full feeling and strength in your limb before you try to stand or walk by yourself.
- If the catheter is in your leg, always use assistive devices such as a knee immobilizer, crutches, or a walker while walking or standing.
- Follow your doctor's instructions about positioning and activity.
- Keep both the bandage and catheter insertion site dry.

## Are there any side effects?

All procedures involve risks, side effects, and possible problems. The most common side effect is short-term pain at the catheter site.

Sometimes, a very small amount of the numbing medication leaks underneath the dressing, but this is nothing to worry about. Other risks include infection, bleeding, and ongoing weakness. It is rare to have serious side effects and problems from this procedure.

## How do I remove the catheter when the pump is empty?

1. Sit down and take off the dressing over the catheter. Do not use scissors.
2. Firmly grasp the catheter near your skin. Slide it out from your skin with gentle, steady pulling. The catheter should come out easily. You should feel very little or no discomfort.
3. If you feel sudden sharp pain when you begin to pull, stop. Call us for instructions (see phone numbers in the "Questions" box).
4. After you remove the catheter, check the tip for a black mark. Call your provider if you do not see the black mark.
5. Place the catheter and pump in the trash.
6. You may place a small bandage over the spot where the catheter was.

To watch a catheter removal video, please visit *www.myon-q/faqs.aspx*.

## Questions?

Your questions are important. Call your doctor or healthcare provider if you have questions or concerns.

- ❑ Harborview Regional Anesthesia Service: Weekdays from 8 a.m. to 5 p.m., call 206.999.0992.
- ❑ After hours and on weekends and holidays, please call the ON-Q 24-hour product support hotline to speak to a registered nurse: 800.444.2728

## When to Call

Call us right away if you have any of these serious symptoms:

- Numb lips
- Metallic taste in your mouth
- Ringing in your ears
- Severe dizziness
- Nausea and vomiting

© University of Washington Medical Center
Published PFES: 2017, 2020, 2022
Clinician Review: 10/2022
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu